# የSY23-24፣ የ'Benjamin Banneker' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት: የመግቢያ (Admission) ሂደት - የደረጃ መጠን (Rubric)

*ለ9 እና 10 ክፍሎች*

**ስለቤንጃሚን ባነከር አካዳሚክ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Benjamin Banneker Academic High School) የመግቢያ (Admissions) መስፈርት:**
በቤንጃሚን ባነከር አካዳሚክ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Benjamin Banneker Academic High School) ውስጥ፣ ለትምህርት ከፍተኛ ስሜት ያላቸውን፣ ለማህበረሰቡ ቁርጠኝነት የሚያሳዩ፣ እና ፈታኝ በሆኑ ነገሮች ውስጥ አልፈው የሚሰሩ፤ ስኬትን ፈላጊዎችን ማግኘት እንፈልጋለን። አብዛኛዎቹ ስኬታማ አመልካቾች፣ ጽናታቸውን በGPA የስኬት ውጤታቸው ላይ ለማስመስከር የቻሉ፤ እንደሆኑ አውቀናል።

**ስለቤንጃሚን ባነከር አካዳሚክ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Benjamin Banneker Academic High School) የመግቢያ (Admissions) ሂደት:**
በቤንጃሚን ባነከር አካዳሚክ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Benjamin Banneker Academic High School) ውስጥ፣ በመጀመሪያ የሁሉንም አመልካቾች ሪፖርት ካርዶች፣ ጽሁፎች (essays)፣ እና ድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) የምንመለከት ይሆናል። በአነስተኛነት መገኘት የሚገባው (minimum) የGPA የውጤት ደረጃ (Score) የለም። በመግቢያ (admissions) ሂደቱ ቀጣይ እርምጃው፣ ምንም አንዱ-አካሉ እንደ የአመልካቹን ብቁነት ብቸኛ መወሰኛነት ጥቅም-ላይ ሳይውል፣ እነዚህ የክፍሎቹ-አካል የሆኑት፣ እያንዳንዳንዳቸው የውጤት-ደረጃዎች ይሰጣቸዋል። ከፍተኛ የውጤት ደረጃን ያስመዘገቡ አመልካቾች፣ በቃለ-መጠይቁ እንዲካፈሉ ይጋበዛሉ።

እያንዳንዱ ክፍሎች፣ ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ መሰረት የደረጃ ውጤት (scored) የሚሰጠው እና የሚመዘን ይሆናል። የተጋበዙ አመልካቾች፣ ብቁነታቸው እንዲታይላቸው ለማድረግ፣ የቃለ-መጠይቁን አካል ማጠናቀቅ አለባቸው። በቃለ-መጠይቁ፣ የሚፈለገውን አነስተኛ (minimum) የውጤት-ደረጃ የሆነውን፤ ከ15 ነጥቦች ውስጥ 9 ያገኙ ሁሉም ተማሪዎች፣ ለመግባት (admission ለማግኘት) ብቁ ተደርገው ይወሰዳሉ። በቃለ-መጠይቁ፣ ከ9 በታች ውጤት ያመጡ አመልካቾች፣ ቃለ-መጠይቁን ጨምሮ አጠቃላይ የተጠራቀመ ውጤቶችን በማመልከቻው ክፍሎች-ውስጥ ባሉት ላይ ሁሉ መሠረት በማድረግ፤ 'ባነከር (Banneker) ያሰላዋል። ሁሉም ብቁ የሆኑ አመልካቾች፤ እኩል የሆነ የደረጃ-አሰጣጥን ያገኛሉ።

| የመግቢያ (Admissions) ክፍሎች | መለኪያ (Weight) | ማስታወሻዎች: |
|---|---|---|

| | | |
|---|---|---|
| የቀለም ትምህርት የመስፈርት ምልከታ<br><br>(GPA) | 20/50 ነጥቦች | የቤንጃሚን ባነከር አካዳሚክ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Benjamin Banneker Academic High School)፣ እንደ የሪፖርት ካርድ ምልከታ በማድረግ፣ የውጤት ደረጃዎችን (GPA)ን ይመለከታል። በአነስተኛነት መገኘት የሚገባው (minimum) GPA ወይም አስፈላጊ የሆነ የፈተና የውጤት ደረጃ የለም፤ ነገር ግን ማመልከቻው፣ ለመግባት (admission) እንዲታይና ከግምት-ውስጥ እንዲገባ ለማድረግ፣ የሪፖርት ካርድ መግባት አለበት።<br><br>በተለምዶ፣ በፕሮግራማችን ስኬታማ የሆኑ ተማሪዎች፣ በሁለቱም ምልከታ በተደረገባቸው የሪፖርት ካርዶች ላይ የ2.5 ወይም ከዚያ በላይ የሆነ GPA አላቸው። ሆኖም፣ አነስተኛ GPAዎች ያሏቸው ተማሪዎች፣ ትክክለኛ የሆነ እርዳታን እና ስልቶችን ሲያገኙ ስኬትን ማግኘት እንደሚችሉ ለማወቅም ችለናል። |
| ጽሁፍ (Essay): በ'My School DC' ማመልከቻ ውስጥ | 6/50 ነጥቦች | በ'My School DC' ማመልከቻ ውስጥ ያለው ጽሁፍ (essay)፤ በፕሮግራማችን ውስጥ የተማሪውን ፍላጎት፣ ለማህበረሰቡ የሚያሳዩትን ቁርጠኝነት፣ እና የግል ጽናታቸውን የማንጸባረቅ ልምዶች ላይ ግምገማ-ለማድረግ ይጠቀምበታል።<br><br>ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ  ትምህርታቸው ወቅት በሙሉ አዘውትረው መፃፍ ይጠበቅባቸዋል፤ ስለሆነም፣ ለጽሁፍ (essay) የውጤት አሰጣጥ ላይ፣ ሰዋሰውና ቃላትን (grammar and vocabulary) ጨምሮ፣ በአፃፃፍ ቴክኒኮች ላይ ያተኮረ ይሆናል። |
| ድጋፍ መስጫዎች (Recommendations) | 24/50 ነጥቦች | የቤንጃሚን ባነከር አካዳሚክ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Benjamin Banneker Academic High School)፣ የተማሪውን የትምህርት ቤት ውስጥ ተሞክሮ የበለጠ ለመረዳት እና የቀለም ትምህርት ባገኙት የውጤት ይዘት ላይ ለመስጠት በማለት፤ የአስተማሪን ድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) ይጠቀማል። አብዛኛዎቹን የባነከር (Banneker) አመልካች የምልከታ መስፈርትን ያካተተ የድጋፍ መስጫዎች (Recommendations)፣ እና እንደ ወሳኝ የሆነ አካል ተደርገው ስለተማሪው ለማወቅ እና ያላቸውን ተሞክሮዎች ለመመልከት ይጠቅማሉ። የቤንጃሚን ባነከር አካዳሚክ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Benjamin Banneker Academic High School)፤ ሦስት (3) የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) - እያንዳንዳቸው በከፍተኛነት (maximum) **8** ነጥቦችን የማስገኘት-አቅም ያላቸውን፣ እንዲቀርብለት-ይጠይቃል። በየግል የገቡ የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) በራሳቸው በኩል እንዲከታተሉ እና የድጋፍ ሰጪውን የኢሚል አድራሻዎች ትክክለኛነት በማረጋገጥ የተማሪውን በእጅጉ የተሟላ ምስል በተቻለ መጠን ለማስገኘት፤ ተማሪዎች እና ቤተሰቦችን ክትትል እንዲያደርጉ አጥብቀን እናበረታታለን። ሆኖም፣ |

| | | |
|---|---|---|
| | | ተማሪዎች ላልተሟሉ ወይም ለጠፉ የድጋፍ መስጫዎች (recommendations) ቅጣት አይደርስባቸውም፤ እና ወደ ቃለ-መጠይቅ ደረጃው -በገባው የድጋፍ መስጫዎች (recommendations) ላይ መሠረት በማድረግ፣ ወደግምገማው እንዲቀጥል ይደረጋል። |
| **ለማለፍ የሚገባው መስፈርት (Threshold criteria) ላይ፣ ከፍተኛ ውጤት ያላቸው አመልካቾች፣ ለመግቢያው (admissions) ሂደት ወደሆነው ወደ ቃለ-መጠይቅ አካሉ እንዲቀጥሉ ይደረጋል።** | | |
| ቃለ-መጠይቅ | 15 ነጥቦች የሚቻል ይሆናል | የቤንጃሚን ባነከር አካዳሚክ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Benjamin Banneker Academic High School)፣ የጋለ ስሜት ያላቸውን እና ለማህበረሰቡ ትጋትን የሚያሳዩ እንዲሁም በመላው ዓለም የተወዳዳሪነት ጽናትን የሚያሳዩ ተማሪዎችን ለይቶ በማውጣት ላይ ከፍተኛ እምነት አለው።<br><br>ወደ ቃለ-መጠይቁ ከተጋበዙ፣ እጩዎቹ ከወላጅ/አሳዳጊ ወይም ከሌላ የቅርብ የቤተሰብ አባል (ከ18 ዓመት በላይ የሆነ) ወይም ሌላ በህይወቱ ውስጥ ጉልህ አስተዋጽዖ ያለው ሰው ጋር (እንደ አሰልጣኝ፣ አማካሪ፣ ወይም የሕይወት መሪ/mentor)፤ ተማሪዎችን በመደበኛነት ከሚረዷቸው ጋር አብሮ መምጣት አለባቸው። እጩዎች፤ በቃለ-መጠይቁ ላይ ለመወያየት እንዲቻል፣ በጣም የቅርብ ጊዜ የሆነ የተማሪ ሪፖርት ካርድን ለማምጣት ማቀድ አለባቸው፤ ነገር ግን ካላመጡ፣ ባለማምጣታቸው የሚደርስባቸው ቅጣት-የለም። አመልካቾችም፤ የጽሁፍ ሃሳብ-መስጫ (writing prompt)ን፣ እንደ የቃለ-መጠይቅ አካል-ሆኖ ማስገባትም አስፈልጋቸዋል።<br><br>በጤና መመሪያ እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት ባደረገ-መልኩ፤ ለSY23-24 ቃለ-መጠይቆች፣ እንደየአስፈላጊነቱ እና በሁኔታዎች-አመላካችነት ላይ መሠረት በማድረግ፣ በርቀት (virtually) የሚሆንበት ሁኔታ ሊኖር ይችል-ይሆናል። የጤና መመሪያን በመከተል እና በመቆጣጠር ላይ፣ ቁርጠኛ ሆኖ መስራቱን -DCPS ይቀጥልበታል። |

| | | |
|---|---|---|
| | | በቃለ-መጠይቁ፣ አስፈላጊ የሆነውን በአነስተኛነት መገኘት የሚገባው (minimum) የውጤት ደረጃን፤ 12 ወይም ከዚያ በላይ ያገኙ ሁሉም ተማሪዎች፣ ለመግባት (admissions) ብቁ ተደርገው ይወሰዳሉ። ትምህርት ቤቱ ዝቅተኛ-የሆነውን የብቁ-ተማሪዎች ቁጥርንን ለማሟላት እንዲችል፤ የውጤት ደረጃቸው በ9-11 መካከል ያሉ ተማሪዎችም ብቁ-ሊሆኑ ይችሉ-ይሆናል። በቃለ-መጠይቁ፣ ከ9 በታች ውጤት ያመጡ ተማሪዎች፣ ቃለ-መጠይቁን ጨምሮ አጠቃላይ የተጠራቀመ ውጤቶችን በአመልካቹ የመማር አካላቶች ውስጥ ባሉት ላይ ሁሉ መሠረት በማድረግ፤ ‘ባነከር (Banneker) ያሰላዋል።<br><br>ሁሉም ብቁ-የሆኑ ተማሪዎች፤ በ ‘My School DC’ ሎተሪ የውሳኔ አሰጣጥ ላይ፣ እኩል-የሆነ የደረጃ-አሰጣጥን ያገኛሉ። |